የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# የሕፃናት መብቶች ስምምነት

**የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 44/25 1989 እ.ኤ.አ.**

## መግቢያ

### የዚህ ስምምነት ተዋዋይ ሀገራት፤

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በታወጁት መርሆዎች መሰረት ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮ ክቡር መሆናቸውንና እኩልና የማይገሰሱ መብቶች ያሏቸው መሆኑን አውቆ መቀበል ለዓለም የነጻነት፣ የፍትሕና የሰላም መሰረት መሆኑን በመገንዘብ፤

የተባበሩት መንግሥታት ሕዝቦች ለመሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችና ለሰው ክብርና ዋጋ ያላቸውን እምነት በቻርተሩ ስለአረጋገጡና ማኅበራዊ እድገትንና የተሻለ የኑሮ ደረጃን በሰፊ ነጻነት ለማራመድ መወሰናቸውን በማጤን፤

እያንዳንዱ ሰው ዘርን ቀለምን፣ ጾታን፣ ቋንቋን፣ ሃይማኖትን፣ ፖለቲካን ወይም ሌላ አመለካከትን፣ ብሔርን ወይም ማኅበራዊ ምንጭን፣ ሀብትን፣ ትውልድን ወይም ሌላ አቋምን በመሳሰሉ ልዩነቶች ሳይደረጉበት በዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች መግለጫ እና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች በተደነገጉት መብቶችና ነጻነቶች የመጠቀም መብት ያለው መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት ማወጁን በማወቅ፤

የተባበሩት መንግሥታት ሕፃናት ልዩ እንክብካቤና እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ማወጁን በማስታወስ፤

ቤተሰብ የሕብረተሰብ መሰረትና ለአባሎቹ፤ በተለይም ለሕፃናት እድገትና ደኅንነት ተስማሚ የሆነ የተፈጥሮ ተቋም በመሆኑ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለበትን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት እንዲችል አስፈላጊው ጥበቃና እገዛ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን በማመን፤

ሕፃኑ ሰብአዊ እድገቱ የተሟላና የተስተካከለ እንዲሆን በቤተሰብ ውስጥ በደስታ፣ በፍቅርና በመግባባት መንፈስ ማደግ እንደሚያስፈልገው በመገንዘብ፤

ሕፃኑ በሕብረተሰብ ውስጥ የራሱን የግል ሕይወት ለመምራት እንዲችል በሚገባ መዘጋጀት ስለአለበት በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በታወጁት መሰረተ-ሃሳቦች በተለይም የሰላም፣ የክብር፣ የመቻቻል፣ የነጻነት፣ የእኩልነትና የመተባበር መንፈስ ሰርፆበት እንዲያድግ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመረዳት፤

ለሕፃናት ልዩ እንክብካቤ የማድረጉ አስፈላጊነት በ1924 እ.ኤ.አ. በወጣው የጄኔቫ የሕፃናት መብቶች መግለጫ፤ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባኤው ኅዳር 20 ቀን 1959 እ.ኤ.አ. በተቀበለው የሕፃናት መብቶች

መግለጫ መመልከቱንና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን (በተለይ በአንቀጽ 23 እና 24) በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃል ኪዳን በተለይ አንቀጽ 10 እና የሕፃናት ደኅንነት በሚመለከታቸው ልዩ ልዩ ተቋሞችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ደንቦችና አግባብ ባላቸው ሰነዶች እውቅና ያገኘ መሆኑን በማስታወስ፤

በሕፃናት መብቶች መግለጫ እንደተመለከተው አንድ ሕፃን በአካልና በአዕምሮ ያልዳበረ በመሆኑ ምክንያት ተገቢ የሆነ የሕግ ጥበቃ ማግኘትን ጨምሮ፤ ከመወለዱ በፊትም ሆነ ከተወለደ በኋላ ልዩ ጥንቃቄና እንክብካቤ እንደሚያሻው በማስታወስ፤

ስለሕፃናት ደኅንነት ጥበቃና እንክብካቤ የወጡትን የማኅበራዊና የሕግ መርሆች መግለጫ፤ በተለይም በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕፃናት ለማሳደጊያ ተቋም የሚሰጡበትንና የጉዲፈቻ ልጅ የሚሆኑበትን ድንጋጌዎች፤ የተባበሩት መንግሥታትን የወጣት ጥፋተኞች የፍትሕ አስተዳደር ደንቦች (የቤይጂንግ ደንቦች) እና በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታና በጦርነት ወቅት ለሴቶችና ለሕፃናት ስለሚደረገው ጥበቃ የወጣውን መግለጫ በማስታወስ፤

በሁሉም ሀገራት እጅግ በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ሕፃናት ስለአሉና እነዚህም ሕፃናት የተለየ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማወቅ፤

የእያንዳንዱ ሕዝብ ልማድና ባህል ለሕፃናት ደኅንነት ጥበቃና የተስተካከለ እድገት የሚኖረውን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት፤

በእያንዳንዱ ሀገር፤ በተለይም በመልማት ላይ ባሉ ሀገራት የሕፃናትን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ዓለም አቀፍ ትብብር የሚያስገኘውን ፋይዳ በመገንዘብ፤ እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡፡

## ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

ሕፃናትን በሚመለከት ሕግ፤ አካለ መጠን የመድረሻው ዕድሜ ከዚህ ያነሰ ካልሆነ በቀር፤ በዚህ ስምምነት “ሕፃን” ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

## አንቀጽ 2

1. ተዋዋይ ሀገራት በግዛቶቻቸው ውስጥ ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ሕፃን በርሱ ወይም በወላጆቹ ወይም በሕጋዊ አሳዳሪው ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከት፣ በብሔር፣ በጎሳ ወይም በማኅበራዊ ዳራ፣ በሀብት፣ በአካል ጉድለት፣ በትውልድ ወይም በሌላ ሁኔታ ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት በዚህ ስምምነት የተዘረዘሩትን መብቶች ሊያከብሩለትና ሊያረጋግጡለት ተስማምተዋል፡፡

2. ተዋዋይ ሀገራት አንድ ሕፃን በወላጆቹ ወይም በሕጋዊ አሳዳሪው ወይም በቤተሰቡ አባላት ሁኔታ ወይም እንቅስቃሴ ወይም በተሰጠ አስተያየት ወይም እምነት ሳቢያ ማንኛቸውም ዓይነት አድልዎ እንዳይደርስበት ወይም ቅጣት እንዳይፈጸምበት ለማረጋገጥ ተገቢ እርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 3

1. በመንግሥት ወይም በግል የማኅበራዊ ደኅንነት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት ሕፃናትን የሚመለከት ማናቸውም እርምጃ ሲወሰድ የሕጻናቱ ጥቅም የሚጠበቅበት ሁኔታ ከሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

2. ተዋዋይ ሀገራት የወላጆችን፣ የሕጋዊ አሳዳሪዎችን ወይም በሕግ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ሌሎች ሰዎች መብቶችና ግዴታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሕፃናት ደኅንነት የሚያስፈልገውን ጥበቃና ጥንቃቄ ሁሉ መደረጉን ለማረጋገጥ፤ ለዚህም ተገቢ የሆኑትን ሕግ የማውጣት እና የአስተዳደር እርምጃዎች ለመውሰድ ተስማምተዋል፡፡

3. ተዋዋይ ሀገራት ለሕፃናት እንክብካቤና ጥበቃ ኃላፊነት ያለባቸው ተቋሞችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አግባብ ባላቸው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች የወጡትን፤ በተለይም የአደጋ መከላከልን፣ የጤና አጠባበቅን፣ የሰው ኃይል ብዛትና ተስማሚነትን፤ እንዲሁም ቁጥጥርን የሚመለከቱ ደረጃዎች መጠበቃቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

## አንቀጽ 4

ተዋዋይ ሀገራት በዚህ ስምምነት እውቅና ያገኙትን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ሕግ የማውጣት፣ የአስተዳደርና ሌሎች እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳሉ፡፡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶችን በሚመለከት ተዋዋይ ሀገራት የሚወስዷቸው እርምጃዎች የየሀገራቸው ሀብት በሚፈቅደው ሙሉ አቅምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በዓለም አቀፍ ትብብር በመታገዝ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5

ተዋዋይ ሀገራት ወላጆች ወይም እንደአግባቡ የቤተዘመድ አባላት ወይም የአካባቢው ባህል ሲፈቅድ ማኅበረሰቡ ሕጋዊ አሳዳሪዎች ወይም ለሕፃኑ አስተዳደር በሕግ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሌሎች ሰዎች ሕፃኑ በዚህ ስምምነት በታወቁት መብቶች ሲጠቀም በየጊዜው ከሚያድገው ችሎታው ጋር የተገናዘበ ተገቢ አመራር በመስጠትና በመቆጣጠር ረገድ ያላቸውን ኃላፊነት፣ መብትና ግዴታ ያከብራሉ፡፡

## አንቀጽ 6

1. ተዋዋይ ሀገራት ማንኛውም ሕፃን በሕይወት የመኖር ተፈጥሯዊ መብት እንዳለው ያውቃሉ፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት አቅም የሚፈቅደውን እርምጃ ሁሉ በመውሰድ የሕፃናትን በሕይወት መኖርንና እድገትን ያረጋግጣሉ፡፡

## አንቀጽ 7

1. ማንኛውም ሕፃን እንደተወለደ ይመዘገባል፤ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮም መጠሪያ ስምና ዜግነት የማግኘት፣ በተቻለ መጠንም ወላጆቹን የማወቅና ከወላጆቹ እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት በተለይ ሕፃኑ ሀገር የለሽ እንዳይሆን በብሔራዊ ሕጋቸው መሰረት፤ እንዲሁም ስለእነዚህ ጉዳዮች አግባብ ባላቸው ዓለም አቀፍ ሰነዶች የተጣሉባቸውን ግዴታዎች በማክበር እነዚህ መብቶች ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

## አንቀጽ 8

1. ተዋዋይ ሀገራት ሕፃኑ ሕገ ወጥ ጣልቃገብነት ሳይደረግበት በሕግ የተረጋገጠው ዜግነቱን፣ ስሙንና የቤተሰብ ግንኙነቱን ጨምሮ ማንነቱን ለመጠበቅ ያለውን መብት ያከብራሉ፡፡
2. ሕፃኑ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ከማንነቱ መገለጫዎች አንደኛውን ወይም ሁሉንም የተነፈገ ሲሆን ማንነቱ በተሟላ አኳኋን በአስቸኳይ እንደገና እንዲረጋገጥ ተዋዋይ ሀገራት ተገቢ የሆነውን ዕርዳታና ጥበቃ ያደርጋሉ፡፡

## አንቀጽ 9

1. ጉዳዩ በፍ/ቤት እንደገና ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች አግባብ ባለው ሕግና ሥነ ሥርዓት መሰረት ለሕፃኑ ጥቅም ሲባል ሕፃኑ ከወላጆቹ ተለይቶ እንዲኖር ካልወሰኑ በቀር፤ ማንኛውም ሕፃን ያለወላጆቹ ፈቃድ ከወላጆቹ እንዳይለይ ተዋዋይ ሀገራት ያረጋግጣሉ፡፡ ሕፃኑ ከቤተሰቦቹ ተለይቶ እንዲኖርና የት ቦታም መኖር እንዳለበት መወሰን ወላጆቹ ሕፃኑን ሲበድሉት ወይም ችላ ሲሉት ወይም ለየብቻው ሲኖሩ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ በጉዳዩ የሚያገባቸው ሁሉ ተካፋይ የመሆንና አስተያየቻውን የመግለጽ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡

3. ተዋዋይ ሀገራት ለሕፃኑ ጥቅምና ደኅንነት ተቃራኒ ሆኖ ካልተገኘ በቀር ከአንደኛው ወይም ከሁለቱም ወላጆቹ ለተለየ ሕፃን በየጊዜው ከወላጆቹ ጋር በግልና በቀጥታ የመገናኘት መብቱን ያከብሩለታል፡፡

4. ሕፃኑ ከወላጆቹ የተለየው ተዋዋይ ሀገር በወሰደው እርምጃ፤ ለምሳሌ ከወላጆቹ አንደኛው ወይም ሁለቱም ወይም ሕፃኑ በመታሰሩ ወይም ወህኒ ቤት በመግባቱ፣ በመሰደዱ፣ ከሀገር በመባረሩ ወይም በመሞቱ፣ (በእስር ቤት በማንኛውም ምክንያት የሚያጋጥም ሞትን ጨምሮ) ሲሆን፤ ለሕፃኑ ወይም ለወላጆቹ አግባብነት ያለው ሲሆን ለሌላ የቤተሰቡ አባል፣ እርምጃዎች የተወሰዱበት የቤተሰብ አባል ያለበትን ቦታ በሚመለከት መረጃ መስጠቱ የሕፃኑን ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ካልሆነ በቀር ተዋዋዩ ሀገር ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተዋዋይ ሀገራት እንዲህ ያለውን ጥያቄ ማቅረብ በራሱ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሰዎች ላይ ችግር የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

## አንቀጽ 10

1. በአንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 1 በተገለጹት የተዋዋይ ሀገራት ግዴታዎች መሰረት አንድ ሕፃን ወይም ወላጆቹ ወደ ተዋዋይ ሀገር በመግባት ወይም ከተዋዋይ ሀገር በመውጣት ቤተሰቡን እንዲቀላቀል በሕፃኑ ወይም በወላጆቹ ማመልከቻ ሲቀርብ ጉዳዩ በቀና መንፈስ፣ በሰብአዊነትና በአፋጣኝ ታይቶ እርምጃ ይወሰዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተዋዋይ ሀገራት እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ማቅረብ በአመልካቾቹና በቤተሰቦቻቸው ላይ ምንም ዓይነት መዘዝ የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

2. የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በቀር፤ ወላጆቹ በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩበት ሕፃን በየጊዜው ከወላጆቹ ጋር በግልና በቀጥታ የመገናኘት መብት አለው፡፡ በአንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 3 የተገለፀውን

የተዋዋይ ሀገራት ግዴታ መሰረት በማድረግ ይህን መብት ተግባራዊ ለማድረግ ተዋዋይ ሀገራት ሕፃኑና ወላጆቹ የራሳቸውን ሀገር ጨምሮ ከማንኛውም ሀገር ለመውጣትና ወደ ራሳቸውም ሀገር ለመግባት ያላቸውን መብት ያከብራሉ፡፡ ከማንኛውም ሀገር የመውጣት መብት ሊገደብ የሚችለው በሕግ በተደነገገውና የሀገራዊ ደኅንነትን፣ የሕዝብን ፀጥታ፣ ጤና ወይም መልካም ሥነ ምግባር ወይም የሌሎችን መብቶችና ነጻነቶች ለማስከበር አስፈላጊ በሆኑትና በዚህ ስምምነት ከተገለጹት ሌሎች መብቶች ጋር በተጣጣመ አኳኋን ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 11

1. ተዋዋይ ሀገራት በሕገ ወጥ መንገድ ሕፃናትን ከሀገር ማስወጣትንና ወደ ሀገር እንዳይመለሱ ማድረግን ለማስቀረት እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡
2. ለዚህም ዓላማ ተዋዋይ ሀገራት ሁለት ወይም ብዙ ተዋዋዮችን ያቀፉ ስምምነቶችን እንዲፈጽሙ ወይም ቀደም ሲል ያሉት ስምምነቶች ተቀባይነት እንዲያገኙ ያበረታታሉ፡፡

## አንቀጽ 12

1. ተዋዋይ ሀገራት ሃሳብ ለማመንጨት ችሎታ ያለው ማንኛውም ሕፃን በሚመለከተው ጉዳይ ሁሉ ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ መብቱን ያረጋግጣሉ፡፡ ሕፃኑ በሚያቀርበውም ሃሳብ ዕድሜውና በአዕምሮ የመብሰል ሁኔታው እየታየ ተገቢው ክብደት ይሰጠዋል፡፡
2. ለዚህ ዓላማ ሲባል በተለይ ሕፃኑን የሚመለከት ጉዳይ በዳኝነት ወይም በአስተዳደር አካል በሚታይበት ጊዜ ከሀገሩ የሥነ ሥርዓት ሕግ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ራሱ በቀጥታ ወይም በእንደራሴ ወይም አግባብ ባለው አካል በኩል የመሰማት ዕድል ይሰጠዋል፡፡

## አንቀጽ 13

1. ሕፃኑ ሃሳቡን የመግለፅ መብት አለው፡፡ ይህም መብት በሀገራት ድንበሮች ሳይወሰን ሁሉንም ዓይነት መረጃዎችና ሃሳቦች በቃል፣ በጽሑፍ ወይም በሕትመት ወይም በሥነ ጥበብ መልክ ወይም ማንኛውም የሕፃኑ ምርጫ በሆነ መገናኛ ዘዴ የመጠየቅ፣ የመቀበልና የማስተላለፍ መብትን ይጨምራል፡፡
2. የዚህ መብት አጠቃቀም የተወሰኑ ገደቦች ሊደረጉበት ይችላል፡፡ ነገር ግን ገደቦቹ አስቀድሞ በሕግ የተደነገጉና፡-

   ሀ/ የሌሎችን መብትና መልካም ስም ለመጠበቅ ወይም፤

   ለ/ የሀገርን ብሔራዊ ጸጥታ ወይም የሕዝብን ሰላም ወይም ጤንነት ወይም ሞራል ለመጠበቅ የሚያስፈልጉት ብቻ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 14

1. ተዋዋይ ሀገራት የሕፃኑን የሃሳብ፣ የኅሊናና የሃይማኖት ነጻነት ያከብራሉ፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት ወላጆች ወይም አግባብ ባለው ሁኔታም ሕጋዊ አሳዳሪዎች ለሕፃናት ከዕድገታቸው ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ ለመብታቸው አጠቃቀም አመራር ለመስጠት ያላቸውን መብትና ኃላፊነት ያከብራሉ፡፡

3. ሃይማኖትን ወይም እምነትን በመግለጽ ነጻነት ላይ የሚደረጉት ገደቦች በሕግ የተደነገጉና የሕዝብን ደኅንነት፣ ፀጥታ፣ ጤንነት ወይም ሞራል ወይም የሌሎችን መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶችን ለማስከበር አስፈላጊ የሆኑ ብቻ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 15

1. ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናት በማኅበር የመደራጀትና ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግ መብት ያላቸው መሆኑን አውቀው ይቀበላሉ፡፡
2. በዴሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ ሀገራዊ ደኅንነትን ወይም የሕዝብን ደኅንነት ወይም ፀጥታ፣ የሕዝብን ጤና ወይም መልካም ሥነ ምግባር ወይም የሌሎች ሰዎችን መብቶችና ነጻነቶች ለመጠበቅ አስፈላጊ ከሆኑትና ከሕግ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ከሚደነገጉት በቀር በእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ላይ ማናቸውም ዓይነት ገደቦች አይደረጉም፡፡

## አንቀጽ 16

1. ማንኛም ሕፃን በግል ኑሮው፣ በቤተሰቡ፣ በመኖሪያ ቤቱ ወይም በሚጻጻፈው ደብዳቤ ሥርዓትን ያልተከተለ ወይም ሕገ ወጥ ጣልቃ ገብነት አይፈጸምበትም፤ ክብሩና መልካም ዝናውም በሕገ ወጥ መንገድ አይደፈርም፡፡
2. ሕፃኑ እንዲህ ካለው ጣልቃ ገብነትና መደፈር የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 17

ተዋዋይ ሀገራት የመገናኛ ብዙኃን የሚያከናውኑትን ጠቃሚ ሥራ በመገንዘብ ሕፃኑ በተለይ ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊና የሞራል ደህንነቱን፣ አካላዊና አዕምሯዊ ጤንነቱን ለመጠበቅ የሚያግዙትን መረጃዎችና ማቴሪያሎች ከተለያዩ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ምንጮች ማግኘት መቻሉን ያረጋግጣሉ፡፡ ለዚህ ተግባራዊነትም ተዋዋይ ሀገራት፡-

ሀ/ የአንቀጽ 29ን መንፈስ በተከተለ መልኩ መገናኛ ብዙኃን ለሕፃናት ማኅበራዊና ባህላዊ ሕይወት የሚጠቅም መረጃና ማቴሪያሎች እንዲያሰራጩ ያበረታታሉ፤

ለ/ የእነዚህን መረጃና ማቴሪያሎች ከተለያዩ ባህላዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ምንጮች መመንጨት፣ ልውውጥና ስርጭትን የሚመለከት ዓለም አቀፍ ትብብር እንዲኖር ያበረታታሉ፤

ሐ/ የሕፃናት መጻሕፍት እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ያበረታታሉ፡፡

መ/ የመገናኛ ብዙኃን ለአናሳ ብሔረሰቦች ወይም ለአካባቢው ነባር ሕዝብ ተወላጅ ሕፃናት የቋንቋ ችግር የተለየ ትኩረት እንዲሰጡ ያበረታታሉ፤

## አንቀጽ 18

1. ተዋዋይ ሀገራት ሁለቱም ወላጆች ለሕፃኑ አያያዝና አስተዳደግ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው የሚለው መርህ ተቀባይነት ማግኘቱን ለማረጋገጥ የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ለሕፃኑ እድገትና አስተዳደግ ወላጆች ወይም እንደሁኔታው ሕጋዊ አሳዳሪዎች ከማንም የበለጠ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፤ ዋናው ትኩረታቸውም የሕፃኑ ጥቅም ይሆናል።

2. በዚህ ስምምነት የተመለከቱትን የሕፃናት መብቶች ተፈጻሚነትን ለማረጋገጥ፣ ሕፃናትን የማሳደግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግና ለማበረታታት ተዋዋይ ሀገራት ለወላጆችና ለሕጋዊ አሳዳሪዎች ተገቢውን ዕርዳታ ያደርጋሉ፤ ለሕፃናት እንክብካቤ የሚሰጡ ተቋሞች፣ ድርጅቶችና አገልግሎቶች መቋቋማቸውንም ያረጋግጣሉ።

3. ተዋዋይ ሀገራት ወላጆቻቸው ሠራተኞች የሆኑ ሕፃናት ለሕፃናት እንክብካቤ በተመደቡ አገልግሎቶችና ድርጅቶች የመጠቀም መብታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳሉ።

## አንቀጽ 19

1. ሕፃኑ በወላጁ/ጆቹ ወይም በሕጋዊ አሳዳሪው/ዎቹ ወይም በማንኛውም ሌላ ሰው ስር በሚገኝበት ጊዜ ማናቸውም ዓይነት አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጥቃት፣ ጉዳት፣ በደል፣ ግዴለሽ ወይም ቸልተኛ አያያዝ፣ ማጉላላት ወይም ብዝበዛና የግብረ ስጋ ግንኙነት በደል ጭምር እንዳይፈጸምበት ተዋዋይ ሀገራት ተገቢ የሆኑ የሕግ ማውጣት አስተዳደራዊ፣ ማኅበራዊና ትምህርታዊ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

2. እንዲህ ያሉት የጥበቃ እርምጃዎች እንደአግባብነቱ ለሕፃኑና ሕፃኑን ለሚንከባከቡ ሰዎች አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጡ ማኅበራዊ ፕሮግራሞችን ለመዘርጋት፤ እንዲሁም ቀደም ብሎ የተገለጹት ተገቢ ያልሆኑ የሕፃናት የአያያዝ ሁኔታዎች እንዳያጋጥሙ ለመከላከል ሲያጋጥሙም የአጥፊውን ማንነት ለመለየት፣ ዘገባ ለማቅረብ፣ ለሚመለከተው ለመምራት፣ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለመከታተልና እንደ አግባብነቱ ፍርድ ቤት ጣልቃ እንዲገባ ለማድረግ የሚያስችሉ አስተማማኝ ሥነ ሥርዓቶችን ያጠቃልላሉ።

## አንቀጽ 20

1. ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው ከቤተሰቡ ለተለየ ወይም ለራሱ ጥቅም ሲባል ከቤተሰቡ መለየት ላለበት ሕፃን መንግሥት ልዩ ጥበቃና ዕርዳታ ያደርጋል፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት በሀገራዊ ሕጎቻቸው መሰረት እንዲህ ዓይነቱ ሕፃን አማራጭ እንክብካቤ ማግኘቱን ያረጋግጣሉ፡፡
3. እንዲህ ዓይነቱ እንክብካቤ ለማደጎ መስጠትን፣ በእስልምና ሕግ መሰረት ካፋላህ ማድረግን፣ ጉዲፈቻ መስጠትን ወይም አስፈላጊ ሲሆን ተስማሚ ለሆነ የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋም መስጠትንና የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል፡፡ መፍትሔዎች በሚጤኑበት ጊዜ የሕፃኑ እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው የማድረግ አስፈላጊነትና ለሕፃኑ የጎሳ፣ የሃይማኖት፣ የባህልና የቋንቋ መሰረት ተገቢ ትኩረት ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 21

ለጉዲፈቻ ሥርዓት እውቅና የሚሰጡ ወይም የሚፈቅዱ ተዋዋይ ሀገራት ከሁሉም በላይ ለሕፃኑ ጥቅም ቅድሚያ መሰጠቱን ያረጋግጣሉ፤ በዚህ መሰረት እነዚህ ሀገራት፡-

ሀ/ ሕፃኑ ለጉዲፈቻ የተሰጠው አግባብ ባላቸው ባለሥልጣናኖች ፈቃድ መሆኑን፤ ባለሥልጣኖቹም አግባብ ባለው ሕግና ሥነ ሥርዓት፤ እንዲሁም አግባብ ባለውና እምነት በሚጣልበት ማንኛውም መረጃ ላይ ተመስርተው የሕፃኑ ወላጆች፣ ዘመዶችና ሕጋዊ አሳዳሪዎች ሁኔታ የሕፃኑን ለጉዲፈቻ መሰጠት የሚፈቅድ መሆኑን መወሰናቸውንና አስፈላጊ ሲሆንም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች አስፈላጊውን የምክር አገልግሎት ካገኙ በኋላ ለጉዲፈቻ ፈቃዳቸውን መስጠታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

ለ/ ሕፃኑን በተወለደበት ሀገር ላለ ማሳደጊያ ተቋም ወይም በጉዲፈቻ ለሚቀበል ቤተሰብ መስጠት ወይም በሌላ ተስማሚ ዘዴ ማሳደግ ካልተቻለ በሌላ ሀገር ውስጥ በጉዲፈቻ መስጠትን እንደ አማራጭ መፍትሔ ይቀበላሉ፡፡

ሐ/ በሌላ ሀገር ውስጥ ለጉዲፈቻ የተሰጠ ሕፃን በሀገር ውስጥ ከሚደረግ ጉዲፈቻ እኩል የሆነ ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግለት መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

መ/ በሌላ ሀገር ውስጥ ለጉዲፈቻ መስጠት በጉዲፈቻው ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑት ሰዎች የማይገባ የገንዘብ ጥቅም ማግኛ እንዳይሆን ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

ሠ/ እንደአግባቡ ከሁለት ወይም ከብዙ ሀገራት ጋር በመስማማት የዚህን አንቀጽ ዓላማዎች ያራምዳሉ፤ ሕፃኑን በሌላ ሀገር ለጉዲፈቻ የመስጠቱ ተግባር በሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ወይም አካላት መከናወኑን ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

## አንቀጽ 22

ተዋዋይ ሀገራትን ጥገኝነት በመጠየቅ ላይ ያለ ሕፃን ወይም አግባብ ባለው ዓለም አቀፍ ወይም ሀገራዊ ሕግና ሥነ ሥርዓት መሰረት ስደተኛ መሆኑ የታወቀ ሕፃን ብቻውን ወይም ከወላጆቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ቢሆንም በዚህ ስምምነትና የተጠቀሱት ሀገራት ተዋዋይ በሆኑባቸው ሌሎች ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶችና ሰብአዊ ሰነዶች ውስጥ በተደነገጉት አግባብ ያላቸው መብቶች እንዲጠቀም ተገቢውን ሰብአዊ ዕርዳታና ጥበቃ ማግኘቱን ለማረጋገጥ ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

ለዚህም ዓላማ ተዋዋይ ሀገራት አግባብ ሆኖ እንደታያቸው የተባበሩት መንግሥታትና ሀገራት በመካከላቸው የፈጠሯቸው ሥልጣን ያላቸው መንግሥታዊ ድርጅቶች ወይም ለተባበሩት መንግሥታት ትብብር የሚያደርጉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲህ ላለው ሕፃን ጥበቃና ዕርዳታ ለማድረግ፤ እንዲሁም ማንኛውም ስደተኛ ሕፃን ከቤተሰቡ ጋር መልሶ ለማገናኘት የሚረዱ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ወላጆቹን ወይም ሌሎች የቤተሰቡን አባላት ለማፈላለግ በሚያደርጉት ጥረት ይተባበራሉ፡፡ ወላጆቹን ወይም ሌሎች የቤተሰቡን አባሎች ለማግኘት ባልተቻለ ጊዜ በዚህ ስምምነት በተደነገገው መሰረት ሕፃኑ በማናቸውም ምክንያት ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው ቤተሰቡን ላጣ ሌላ ሕፃን የሚደረግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

## አንቀጽ 23

1. ተዋዋይ ሀገራት የአዕምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ የሆነ ሕፃን ሰብአዊ ክብርን በሚያረጋግጥ፣ በራስ መተማመንን በሚያበረታታና በማኅበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው በሚያመቻች ሁኔታ የተሟላና ጥሩ ሕይወት መኖር እንደሚገባው ይገነዘባሉ፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት የአዕምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ የሆነ ሕፃን ልዩ እንክብካቤ ለማግኘት ያለውን መብት አውቀው ይቀበላሉ፤ የሀብት አቅማቸው በፈቀደ መጠንም ማመልከቻ ሲቀርብ ለሕፃኑና እርሱን የመንከባከብ ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎች ሕፃኑና ወላጆቹ ወይም ሕፃኑን የሚንከባከቡ ሰዎች ከሚገኙበት ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሆነ ዕርዳታ እንዲሰጥ ያበረታታሉ፤ መሰጠቱንም ያረጋግጣሉ፡፡
3. የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኛ የሆነን ሕፃን ልዩ ፍላጎት በመገንዘብ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚደረግ ዕርዳታ የወላጆችን ወይም የአሳዳሪዎችን የገንዘብ አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በተቻለ መጠን በነፃ የሚሰጥና የሕፃኑን ችሎታ ለማዳበር፣ ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሎ እንዲኖር ለማስቻልና ባህላዊና መንፈሳዊ ዕድገቱ የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ አመቺ የሆነ ትምህርት፣ ስልጠና፣ የጤናና የተሐድሶ አገልግሎት፣ የሥራ ስምሪት ዝግጅትና የመዝናኛ አገልግሎት ማግኘቱን ለማረጋገጥ የታቀደ መሆን አለበት፡፡

4. ተዋዋይ ሀገራት የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኞች ሕፃናትን በሚመለከት በሕክምና መስክ በሽታን ስለመከላከል ዘዴዎች፣ ስለ ሥነ ሕክምና፣ በሥነ ልቦናና በተግባር ማከምን በተመለከተ የመረጃዎች ልውውጥን በዓለም አቀፍ የትብብር መንፈስ ያበረታታሉ፡፡ ይህም ተዋዋይ ሀገራት በዚህ ዘርፍ ያላቸውን ችሎታና ሙያ ለማሻሻልና ልምድ ለማስፋት የሚያግዙ የተሐድሶ ዘዴዎችን፣ የትምህርትና የሞያ ስልጠና አገልግሎቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማሰራጨትንና ማግኘትን ይጨምራል፡፡ በዚህ ረገድ በመልማት ላይ ያሉ ሀገራት ላሏቸው ፍላጎቶች ልዩ ግምት መስጠት አለበት፡፡

## አንቀጽ 24

1. ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናት ሊደረስበት የሚቻለው ከሁሉም የተሻለ የሕክምናና የተሐድሶ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ያላቸውን መብት ይገነዘባሉ፡፡ ተዋዋይ ሀገራት ማንኛውም ሕፃን እንዲህ ያሉትን የጤና አገልግሎቶች የማግኘት መብቱን እንደማይነፈግ ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

2. ተዋዋይ ሀገራት ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ለማዋል ይተጋሉ፤ በተለይም፡-

ሀ/ የጨቅላ ሕፃናትንና የሕፃናትን ሞት መጠን ለመቀነስ፤

ለ/ ለመሰረተ ጤና እንክብካቤ እድገት ቅድሚያ በመስጠት ለሁሉም ሕፃናት አስፈላጊ የሕክምናና የጤና አገልግሎቶች መሰጠቱን ለማረጋገጥ፤

ሐ/ የአካባቢ መበከል በጤና ላይ የሚያስከትለውን አደጋና ጠንቅ ከግምት ውስጥ በማስገባት በመሰረተ ጤና እንክብካቤ መዋቅር ጭምር ንፁህ የመጠጥ ውኃንና አልሚ ምግቦችን በማቅረብና እንዲሁም በቀላሉ የሚገኝ ቴክኖሎጂን መጠቀም ጨምሮ በሽታንና የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን ለመከላከል፤

መ/ እናቶች ተገቢ ቅድመ ወሊድና ድኅረ ወሊድ የጤና አገልግሎት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፤

ሠ/ ማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል በተለይ ወላጆችና ሕፃናት ስለ ሕፃናት ጤናና አመጋገብ፣ ጡት ማጥባት ስለሚሰጠው ጥቅም፣ ስለ ግልና የአካባቢ ንጽሕና፤ እንዲሁም ከአደጋ ስለመከላከል መረጃ እንዲያገኙ፣ እንዲማሩና በአገኙት መሰረታዊ ዕውቀት እንዲጠቀሙ አስፈላጊው ድጋፍ መሰጠቱን ለማረጋገጥ፤

ረ/ በሽታን የመከላከል እና የጤና አጠባበቅ ዘዴን ለማሻሻል ለወላጆች የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትና አገልግሎት እንዲስፋፋ ለማድረግ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

3. ተዋዋይ ሀገራት ለሕፃናት ጤና ጠንቅ የሆኑ ባህላዊ ልምዶችን ለማስወገድ ተገቢና ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡
4. ተዋዋይ ሀገራት በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን መብት ሙሉ በሙሉ ደረጃ በደረጃ ሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ዓለም አቀፍ ትብብርን ያበረታታሉ፡፡ በዚህ ረገድ በመልማት ላይ ላሉ ሀገራት ፍላጎቶች ልዩ ግምት ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 25

ተዋዋይ ሀገራት የአካል ወይም የአዕምሮ እንክብካቤ፣ ጥበቃ ወይም ሕክምና እንዲደረግለት ሥልጣን ባለው አካል ውሳኔ በአንድ በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ የተደረገ ሕፃን የአያያዙ ሁኔታ እና በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ የተደረገበት ሁኔታዎች በየጊዜው እንዲገመገሙለት ለማድረግ ያለውን መብት ያውቃሉ፡፡

## አንቀጽ 26

1. ተዋዋይ ሀገራት እያንዳንዱ ሕፃን ማኀበራዊ መድህንን ጨምሮ በማኀበራዊ ዋስትና ለመጠቀም ያለውን መብት ያውቃሉ፤ ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችንም በየሀገራቸው ሕግ መሰረት ይወስዳሉ፡፡
2. እነዚህ ጥቅሞች መስጠት ያለባቸው እንደአግባብነቱ የሕፃኑንና ለሕፃኑ ቀለብ የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች ሀብትና ሁኔታ፤ እንዲሁም ጥቅሙ እንዲሰጠው በሕፃኑ ወይም በእርሱ ስም ለቀረበው ማመልከቻ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

## አንቀጽ 27

1. ተዋዋይ ሀገራት እያንዳንዱ ሕፃን ለአካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ መንፈሳዊ፣ ኅሊናዊና ማኀበራዊ እድገቱ ተስማሚ የሆነ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብት እንዳለው ይገነዘባሉ፡፡
2. ወላጆች ወይም ለሕፃኑ አስተዳደግ ኃላፊነት ያለባቸው ሌሎች ሰዎች ችሎታቸውና የገንዘብ አቅማቸው በሚፈቅደው መጠን ለእድገቱ አስፈላጊ የሆኑ የኑሮ ሁኔታዎች የማመቻቸት የመጀመሪያ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. ወላጆችና ለሕፃኑ ኃላፊነት ያለባቸው ሌሎች ሰዎች ይህን መብት ሥራ ላይ እንዲያውሉ ለማገዝ ተዋዋይ ሀገራት በየሀገራቸው ሁኔታዎችና በአቅማቸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፤ በተለይ በምግብ፣ በልብስና በመጠለያ ረገድ ፍላጎት ሲኖር የማቴሪያል ዕርዳታ ይሰጣሉ፣ የዕርዳታ ፕሮግራሞችንም ያዘጋጃሉ፡፡

4. በተዋዋዩ ሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ካሉት ወላጆቹ ወይም ለሕፃኑ ገንዘብ የመስጠት ኃላፊነት ካለባቸው ሌሎች ሰዎች ለሕፃኑ ቀለብ ለማስገኘት ተዋዋይ ሀገራት ማናቸውንም ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ። በተለይ ለሕፃኑ ማሳደጊያ ገንዘብ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ሰው ሕፃኑ ከሚገኝበት ሀገር ውጭ የሚኖር ከሆነ አባል ሀገራት ለዚህ ተግባር የሚያገለግሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ማድረግን ያበረታታሉ፤ ሌሎችም አግባብ ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ያመቻቻሉ።

## አንቀጽ 28

1. ተዋዋይ ሀገራት የሕፃናትን የመማር መብት ያውቃሉ። ይህንን መብት ደረጃ በደረጃና ለሁሉም እኩል ዕድል መስጠት በሚለው መርህ ላይ በመመስረት ሥራ ላይ ለማዋል በተለይ፡-

   ሀ/ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ግዴታ እንዲሆንና ለሁሉም በነፃ እንዲዳረስ ያደርጋሉ።

   ለ/ አጠቃላይ ትምህርትንና የሙያ ትምህርትን ጨምሮ ልዩ ልዩ ዓይነት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች እንዲስፋፉ ያበረታታሉ፤ እነዚህ የትምህርት ዓይነቶች ለእያንዳንዱ ሕፃን እንዲዳረሱ ያደርጋሉ፤ በተጨማሪም ለችግረኛ ተማሪዎች ነጻ ትምህርት መስጠትን፣ የገንዘብ ዕርዳታ ማድረግን የመሳሰሉ ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

   ሐ/ በማናቸውም ተገቢ መንገድ ችሎታን መሰረት በማድረግ የከፍተኛ ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋሉ።

   መ/ የትምህርትና የሙያ መረጃዎችና መመሪያዎች ለሁሉም ሕፃናት እንዲዳረሱ ያደርጋሉ።

   ሠ/ ሕፃናት ሳይስተጓጎሉ በትምህርት ገበታ ላይ እንዲገኙና ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥር እንዲቀንስ ለማድረግ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

2. ተዋዋይ ሀገራት የትምህርት ቤት ሥነ ሥርዓት አጠባበቅ ከሕፃናት ሰብአዊ ክብርና ከዚህ ስምምነት ጋር በተጣጣመ አኳኋን መመራቱን ለማረጋገጥ ማናቸውንም ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ።

3. ተዋዋይ ሀገራት ትምህርትን በሚመለከቱ ጉዳዮች፤ በተለይም ከዓለም ድንቁርና እና መሃይምነትን ጨርሶ ለማጥፋት አስተዋጽዖ ለማድረግ ሳይንሳዊና፣ ቴክኒካዊ እውቀትን ተደራሽ ለማድረግና ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲዳረሱ በማመቻቸት ረገድ ዓለም አቀፍ ትብብር እንዲኖር ያበረታታሉ። በዚህ ረገድ በመልማት ላይ ያሉ ሀገራት ያሏቸው ፍላጎቶች ልዩ ግምት ይሰጣቸዋል።

## አንቀጽ 29

1. ተዋዋይ ሀገራት ለሕፃናት የሚሰጠው ትምህርት ወደሚከተሉት አቅጣጫዎች እንዲያተኩር ተስማምተዋል፡፡

ሀ/ የሕፃኑን ስብእና፣ ተሰጥኦ፣ የአዕምሮርና የአካል ችሎታ በተሟላ አኳኋን ለማዳበር፤

ለ/ ሰብአዊ መብቶችንና መሰረታዊ ነጻነቶችን፤ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ውስጥ የተደነገጉትን መርሆዎች ማክበርን ለማረጋገጥ፤

ሐ/ ወላጆችን፣ የራስን ባህል፣ ቋንቋ፣ ወግና ሥርዓት፣ የሚኖሩበትን ወይም የመጡበትን ሀገር ብሔራዊ ወጎችንና ሥርዓቶችን፤ እንዲሁም ከራሳቸው የሚለዩ ሥልጣኔዎችን የማክበር ዝንባሌን ለማዳበር፤

መ/ ሁሉም ሕዝቦች፣ ጎሳዎች፣ ብሔሮችና የሃይማኖት ቡድኖች፤ እንዲሁም የሀገሩ ቀደምት ነዋሪዎች፣ ተወላጆች በሚኖሩበት ነፃ ሕብረተሰብ ውስጥ በመግባባት፣ በሰላም፣ በመቻቻል፣ የጾታ እኩልነትን በጠበቀና በወዳጅነት መንፈስ መኖር እንዲችሉ ሕፃናትን ኃላፊነት ላለበት ሕይወት ለማዘጋጀት፤

ሠ/ የተፈጥሮ አካባቢን የማክበር ዝንባሌን ለማዳበር፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገጉት መርሆዎችና ሀገሩ የትምህርት አሰጣጥን በሚመለከት በየጊዜው የሚያወጣቸው ደረጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የዚህ አንቀጽ ወይም የአንቀጽ 28 ማንኛውም ክፍል ግለሰቦች ወይም የተለያዩ አካላት ወይም የትምህርት ተቋማት ለማቋቋምና ለመምራት ባላቸው መብት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት እንደሚያስችል ተደርጎ አይተረጎምም፡፡

## አንቀጽ 30

የሕዝብ ቁጥራቸው አናሳ የሆኑ ጎሳዎች፣ የሃይማኖት ወይም የቋንቋ ቡድኖች ወይም የሀገሩ ቀደምት ነዋሪ ሕዝቦች ተወላጆች ባሉባቸው ሀገራት የእንዲህ ዓይነቱ በቁጥር አናሳ የሆነ ቡድን ወገን የሆነ ወይም የሀገሩ ቀደምት ነዋሪ ሕዝቦች ተወላጅ የሆነ ሕፃን ከራሱ ቡድን አባላት ጋር በሕብረት የራሱን ባህል ለመከተል፣ ሃይማኖቱን ለመግለጽና ሥርዓቱን ለማክበር፤ እንዲሁም በራሱ ቋንቋ ለመጠቀም ያለው መብት አይነፈግም፡፡

## አንቀጽ 31

1. ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናት ለማረፍና ለመዝናናት፣ ለዕድሜያቸው ተስማሚ በሆነ ጨዋታና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ለመካፈል፣ በባህልና ሥነ ጥበብ መስክ በነጻነት ለመሳተፍ ያላቸውን መብት ያውቃሉ፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናት በባህልና ሥነ ጥበብ መስክ ለመሳተፍ ያላቸውን መብት በማክበርና በመደገፍ በባህል፣ በሥነ ጥበብና በመዝናኛ ፕሮግራሞች ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ ዕድል ለሁሉም በእኩልነትና ተስማሚ በሆነ አኳኋን እንዲዳረስ ያበረታታሉ፡፡

## አንቀጽ 32

1. ተዋዋይ ሀገራት ሕፃኑ ከኢኮኖሚ ብዝበዛና ለአደጋ ከሚያጋልጥ ወይም የሕፃኑን ትምህርት ከሚያደናቅፍ ወይም ለሕፃኑ ጤና ወይም ለአካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሞራላዊ ወይም ማኅበራዊ እድገቱ ጎጂ ከሆነ ሥራ ጥበቃ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት ይህ አንቀጽ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ሕግ ያወጣሉ፤ የአስተዳደር፣ የማኅበራዊና ትምህርት ነክ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡ ለዚህ ዓላማና በሌሎች ዓለም አቀፍ ሰነዶች የተደነገጉትን አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ተዋዋይ ሀገራት በተለይ፡-

   ሀ/ ዝቅተኛ የቅጥር ዕድሜን ወይም ዕድሜዎችን ይወስናሉ፤

   ለ/ የሥራ ሰዓትንና የቅጥር ሁኔታዎችን የሚመለከት ተገቢ ደንብ ያወጣሉ፤

   ሐ/ ይህ አንቀጽ በሚገባ በሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ተገቢ ቅጣቶችን ወይም ሌሎች እርምጃዎችን ይደነግጋሉ፤

## አንቀጽ 33

ተዋዋይ ሀገራት አግባብ ባላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሱስ የሚያስይዙ ወይም አዕምሮን የሚያደነዝዙ ተብለው የሚታወቁ ነገሮች ሕፃናት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ እንዳይጠቀሙ ለማድረግ፤ እንዲሁም ሰዎች ሕፃናትን እነዚህን ነገሮች በማምረት ወይም በማሰራጨት ተግባር ላይ እንዳያሰማሩ ለመከልከል የሕግ፣ የአስተዳደር፣ የማኅበራዊና የትምህርት እርምጃዎችን ጨምሮ ማንኛውንም ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

## አንቀጽ 34

ተዋዋይ ሀገራት በሕፃናት ላይ ማንኛውም ዓይነት የወሲብ ብዝበዛና በደል እንዳይፈፀም ጥበቃ ለማድረግ ተስማምተዋል፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት ሲባል ተዋዋይ ሀገራት በተለይ፡-

ሀ/ ሕፃናት ሕገ ወጥ የወሲብ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ማነሳሳትንና ወይም ማስገደድን፤

ለ/ ሕፃናትን በሴተኛ አዳሪነት ወይም በሌላ ሕገ ወጥ የወሲብ ግንኙነት ተግባር ላይ አሰማርቶ መበዝበዝን፤

ሐ/ ሕፃናትን በአስነዋሪ (ፖርኖግራፊ) ትርዒቶችና ማቴሪያሎች በመጠቀም መበዝበዝን ለመከላከል ማናቸውንም አግባብ ያላቸው ሀገራዊና የሁለትዮሽ ወይም ከዚህ በላይ በሆኑ ሀገራት ትብብር ላይ የተመሰረቱ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

## አንቀጽ 35

ተዋዋይ ሀገራት ለማንኛውም ዓላማ ወይም በማንኛውም መልክ ሕፃናትን የመጥለፍ፣ የመሸጥ ወይም በሕፃናት የመነገድ ተግባርን ለመከላከል ማንኛውንም አግባብ ያላቸው ሀገራዊና የሁለትዮሽ ወይም በብዙ ሀገራት ትብብር ላይ የተመሰረቱ እርምጃዎችን ይይወስዳሉ።

## አንቀጽ 36

ተዋዋይ ሀገራት ሕፃናትን ለደኅንነታቸው ጠንቅ ከሆኑ ሌሎች ማናቸውም የብዝበዛ ዓይነቶች ይጠብቃሉ።

## አንቀጽ 37

ተዋዋይ ሀገራት የሚከተሉት መከበራቸውን ያረጋግጣሉ፤

ሀ/ ማንኛውም ሕፃን በሚያሰቃይ ወይም ጭካኔ በተሞላበት፣ ኢ-ሰብአዊ በሆነ ወይም ሰብአዊ ክብርን በሚያዋርድ ቅጣት አይቀጣም። ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች ለፈጸሟቸው ወንጀሎች የሞት ወይም የመፈታት ዕድል የሌለው የዕድሜ ልክ እስራት ቅጣት አይወሰንም።

ለ/ ማንኛውም ሕፃን በሕገ ወጥ ወይም በዘፈቀደ አሰራር ነጻነቱን አይገፈፍም። አንድ ሕፃን የሚያዘው፣ በቁጥጥር ሥር የሚውለውና የሚታሰረው በሕግ መሰረት ነው፤ እስራቱም እንደመጨረሻ አማራጭ ብቻ ተፈፃሚ የሚሆንና ተገቢ ከሆኑት አማራጮች ከሁሉም ለሚያጥረው ጊዜ የሚቆይ መሆን አለበት።

ሐ/ ነጻነቱን እንዲያጣ የተደረገ ማንኛውም ሕፃን ዕድሜው የሚጠይቃቸውን ፍላጎቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ለሰብአዊ ፍጡር ሊሰጥ በሚገባው ክብርና ርህራሄ መያዝ አለበት። በተለይም ከአዋቂዎች ቢለይ ለሕፃኑ የማይበጅ ካልሆነ በቀር ነፃነቱን እንዲያጣ የተደረገ ማንኛውም ሕፃን ከአዋቂዎች እንዲለይ ይደረጋል፤ ልዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በቀርም በመልዕክት ልውውጥና በጉብኝቶች አማካይነት ከቤተሰቦቹ ጋር ግንኙነት የማድረግ መብቱ ይጠበቃል።

መ/ ማንኛውም ነጻነቱን እንዲያጣ የተደረገ ሕፃን የሕግና ሌላ አግባብ ያለው እርዳታ በአፋጣኝ የማግኘትና ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ሥልጣን ካለው ነፃና ገለልተኛ ከሆነ ባለሥልጣን ዘንድ ቀርቦ

ነጻነቱን ያጣበትን ጉዳይ ሕጋዊነት የመጠየቅና በጉዳዩ ላይም ፈጣን ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 38

1. ተዋዋይ ሀገራት በጦርነት ጊዜ በእነሱ ላይ ተፈጻሚነትና አግባብነት ያላቸውን ሕፃናትን የሚመለከቱ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ አያያዝ ሕጎችና ደንቦችን ያከብራሉ፤ መከበራቸውንም ያረጋግጣሉ፡፡
2. ተዋዋይ ሀገራት ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች በጦርነት ቀጥታ ተካፋይ እንዳይሆኑ የሚቻለውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ፡፡
3. ተዋዋይ ሀገራት ዕድሜያቸው 15 ዓመት ያልሞላ ሰዎችን ለጦር ኃይሎቻቸው ከመመልመል ይታቀባሉ፡፡ ዕድሜያቸው በ15 እና በ18 ዓመት መካከል ያሉትን በሚመለምሉበት ጊዜም በዕድሜያቸው ከፍ ላሉት ቅድሚያ ለመስጠት ጥረት ያደርጋሉ፡፡
4. ተዋዋይ ሀገራት በጦርነት ጊዜ የሲቪሉን ሕዝብ ደኅንነት ለመጠበቅ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ አያያዝ ሕግ ባለባቸው ግዴታ መሰረት፤ ጦርነት ችግር ለፈጠረባቸው ሕፃናት ጥበቃና ጥንቃቄ መደረጉን ለማረጋገጥ የተቻለውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ፡፡

## አንቀጽ 39

ተዋዋይ ሀገራት የእንክብካቤ እጦት፣ የብዝበዛ፣ የመጉላላት፣ የስቃይ ወይም የማናቸውም ዓይነት ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብአዊ የሆነ፤ ወይም ሰብአዊ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ፣ ቅጣት ወይም የጦርነት ሰለባ የሆነ ሕፃን በአካልና በሥነ ልቦና ከደረሰበት ጉዳት እንዲያገግምና ከሕብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀል ለማድረግ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ በዚህ ዓይነት ከጉዳቱ እንዲያገግም የማድረጉና ወደ ሕብረተሰቡ የመቀላቀሉ ጉዳይ ለሕፃኑ ጤንነት ተስማሚና ለራስ ዋጋና ክብር የመስጠት ስሜትን ለማዳበር አመቺ በሆነ አካባቢ ይከናወናል፡፡

## አንቀጽ 40

1. ተዋዋይ ሀገራት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሷል የተባለ፣ ጥሷል ተብሎ የተከሰሰ ወይም መጣሱ የታወቀ ማንኛውም ሕፃን ስለራሱ ክብርና ዋጋ ሊኖረው ከሚገባው ስሜት ጋር ተስማሚ የሆነ፤ ለሌሎች ሰዎች ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነጻነቶች ክብር መስጠትን የሚያጠናክር፣ ዕድሜውን እንዲሁም ከሕብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀልና በሕብረተሰብ ውስጥ ገንቢ ሚና እንዲኖረው እገዛ የማድረግን አስፈላጊነት ግምት ውስጥ ያስገባ አያያዝ የማግኘት መብቱን ያውቃሉ፡፡

2. ለዚህ ዓላማ ከግብ መድረስ ተዋዋይ ሀገራት አግባብ ያላቸውን የዓለም አቀፍ ሰነዶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ በተለይ የሚከተሉትን ያረጋግጣሉ፤

ሀ/ ማንኛውም ሕፃን አንድ ድርጊት በፈፀመ ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ በሀገራዊ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ ያልተከለከለ ከነበረ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሷል ተብሎ የማይከሰስ ወይም እንደጣሰ የማይቆጠር መሆኑን፤

ለ/ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሷል የተባለ ወይም በመጣሱ የተከሰሰ ማንኛውም ሕፃን ቢያንስ የሚከተሉት ዋስትናዎች ይኖሩታል፡፡

1. በሕግ መሰረት ጥፋተኛነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ ንጹሕ ሆኖ የመገመት፤
2. የቀረበበትን ክስ በፍጥነትና በቀጥታ፣ አስፈላጊ ሲሆንም በወላጆቹ ወይም በሕጋዊ አሳዳሪዎቹ በኩል የማወቅ፤ እንዲሁም ለክሱ መከላከያ አዘጋጅቶ ለማቅረብ የሕግ ወይም አግባብነት ያለው ሌላ ዕርዳታ የማግኘት፤
3. ሥልጣን ባለውና ነጻና ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል በሕግ መሰረት ጉዳዩ ሳይዘገይና በትክክል እንዲታይለትና እንዲወሰንለት፤ ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜም የሕግ ወይም አግባብ ያለው ሌላ እርዳታ የማግኘት፤ እንዲሁም በተለይ ዕድሜውንና ያለበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ለሕፃኑ የማይጠቅም ሆኖ ካልተገኘ በቀር ወላጆቹ ወይም የሕግ እንደራሴዎቹ እንዲገኙለት፤
4. የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ጥፋተኛነቱን እንዲያምን ያለመገደድ፤ የቀረቡበትን ምስክሮች የመጠየቅ ወይም ጥያቄዎች እንዲቀርቡላቸው የማድረግና እርሱ የጠራቸው ምስክሮችም ከሌሎች እኩል እንዲሰሙለትና እንዲጠየቁለት የማድረግ፤
5. የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን ጥሷል ተብሎ ከተፈረደበት ይህ ፍርድና በፍርዱ መሰረት የተወሰዱበት እርምጃዎች ሁሉ ሥልጣን ባለውና ነጻና ገለልተኛ በሆነ የበላይ ባለሥልጣን ወይም የዳኝነት አካል በሕግ መሰረት እንዲመረመርለት የማድረግ፤
6. የሚሰራበትን ቋንቋ ለመረዳት ወይም ለመናገር የማይችል ከሆነ የአስተርጓሚ ዕርዳታ በነፃ የማግኘት፤
7. ጉዳዩ በሚታይበት በየትኛውም ደረጃ የግል ነፃነቱ እንዲከበርለት ማድረግ፤

3. ተዋዋይ ሀገራት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሰዋል የተባሉ፣ ጥሰዋል ተብለው የተከሰሱ ወይም መጣሳቸው የታወቀ ሕፃናትን የሚመለከቱ ሕጎች፣ ሥነ ሥርዓቶች፣ መሥሪያ ቤቶችና ተቋሞች እንዲኖሩ ለማድረግ በተለይም፡-

ሀ/ ሕፃናት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የመጣስ ችሎታ እንደሌላቸው ተደርገው የሚቆጠሩበትን ዝቅተኛ ዕድሜ ለመወሰን፤

ለ/ ተገቢና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብአዊ መብቶችና የሕግ ጥበቃዎች እስከተከበሩ ድረስ እንዲህ የመሰሉ ሕፃናትን በተመለከተ ከፍርድ ሂደት ውጭ እርምጃዎች የሚወስዱበትን ሥርዓት ለመዘርጋት፤

4. የተለያዩ እንክብካቤዎች፣ የአመራርና የቁጥጥር ትዕዛዞች፣ የምክር አገልግሎቶች፣ አመክሮ፣ የማሳደጊያ ቤት እንክብካቤ፣ ትምህርትና የሞያ ስልጠና ፕሮግራሞች፤ እንዲሁም የተቋሞች እንክብካቤን የሚተኩ ሌሎች ልዩ ልዩ አማራጮች እንዲኖሩ ያደርጋሉ፤ እነዚህም ለሕፃናት ደኅንነት አስተማማኝ የሆኑና ከሚገኙበት ሁኔታና ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው።

## አንቀጽ 41

ይህ ስምምነት የሕፃናትን መብት ሥራ ላይ ለማዋል ይበልጥ አመቺ የሆኑና (ሀ) ስምምነቱን በተቀበለ ሀገር ሕግ፤ ወይም (ለ) በዚያ ሀገር ላይ ተፈጻሚነት ባለው ዓለም አቀፍ ሕግ የተገለጹትን ድንጋጌዎች የሚነካ አይሆንም።

# ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 42

ተዋዋይ ሀገራት የስምምነቱን መርሆዎችና ድንጋጌዎች በአዋቂዎችና በሕፃናት ዘንድ በሰፊው እንዲታወቁ ለማረደግ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ።

## አንቀጽ 43

1. ተዋዋይ ሀገራት በስምምነቱ የገቧቸውን ግዴታዎች ለመፈጸም ያደረጉትን እርምጃ ለመገምገም የሚከተሉትን ተግባሮች የሚያከናውን አንድ የሕፃናት መብቶች ኮሚቴ ይቋቋማል።
2. ኮሚቴው ከፍተኛ ሥነ ምግባርና በስምምነቱ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ የታወቀ ችሎታ ያላቸውን አስር ኤክስፐርቶች በአባልነት የሚይዝ ይሆናል። የኮሚቴው አባሎች ከተዋዋይ ሀገራት ዜጎች መካከል በተዋዋዮቹ ሀገራት ተመርጠው በግላቸው ያገለግላሉ። በምርጫው ወቅት ፍትሐዊ የሆነ ጂኦግራፊያዊ ስብጥር እንዲኖርና የታወቁ የሕግ ሥርዓቶች እንዲወከሉ ትኩረት ይሰጣል።
3. የኮሚቴው አባሎች በተዋዋይ ሀገራት ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል በምስጢራዊ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ይመረጣሉ። እያንዳንዱ ሀገር ከዜጎች መካከል ለምርጫው አንድ ዕጩ ማቅረብ ይችላል።
4. የኮሚቴው አባሎች የመጀመሪያ ምርጫ ይህ ስምምነት በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሚፈጸም ይሆናል። እያንዳንዱ ምርጫ ከሚደረግበት ቀን ቢያንስ አራት ወር አስቀድሞ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለተዋዋይ ሀገራት

ዕጩዎቻቸውን በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያሳውቁ በደብዳቤ ይጠይቃል፡፡ በማስከተልም ዋና ጸሐፊው የሁሉንም ዕጩዎች ስም ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተልና ከየትኛው ሀገር በዕጩነት እንደቀረቡ አዘጋጅቶ ለተዋዋይ ሀገራት እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

5. ምርጫዎቹ የሚደረጉት በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በሚጠሩና ተዋዋይ ሀገራት በድርጅቱ ዋና ጽሕፈት ቤት(ጽ/ቤት) በሚያደርጓቸው ስብሰባዎች ነው፡፡ ከተዋዋይ ሀገራት ሁለት ሦስተኛው በስብሰባዎቹ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ሲሆን፤ በስብሰባዎቹ ተገኝተው ድምፅ ከሰጡት ተዋዋይ ሀገራት ተወካዮች ከግማሽ በላይና በከፍተኛ ድምፅ የተደገፉት ሰዎች የኮሚቴው አባሎች ሆነው ይመረጣሉ፡፡
6. የኮሚቴው አባሎች ለአራት ዓመታት የሥራ ዘመን ይመረጣሉ፡፡ እንደገና በዕጩነት ከቀረቡም ዳግመኛ ለመመረጥ ሊወዳደሩ ይችላሉ፡፡ የአምስቱ የኮሚቴው አባሎች የሥራ ዘመን የመጀመሪያው ምርጫ በተደረገ በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ ይፈጸማል፡፡ የመጀመሪያው ምርጫ እንደተደረገ ወዲያውኑ የስብሰባው ሊቀመንበር በሚያወጣው ዕጣ የእነዚህ አምስት አባላት ስም ይለያል፡፡
7. የኮሚቴው የማጽደቅ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አንድ የኮሚቴ አባል የሞተ ወይም በራሱ ፈቃድ ሥራውን የለቀቀ ወይም በማናቸውም ምክንያት የኮሚቴውን ሥራ ማከናወን የማይችል መሆኑን የገለጸ እንደሆነ፤ ለቀሪው የሥራ ዘመን የሚያገለግል ምትክ ኤክስፐርት በዕጩነት ያቀረበው ሀገር ከዜጎቹ መካከል መርጦ ይሾማል፡፡
8. ኮሚቴው የራሱን የሥነ ሥርዓት ደንቦች ያወጣል፡፡
9. ኮሚቴው የራሱን ሹማምንት ለሁለት ዓመት የሥራ ጊዜ ይመርጣል፡፡
10. የኮሚቴው ስብሰባዎች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት ወይም ኮሚቴው በሚወስነው ሌላ ተስማሚ ቦታ ይደረጋሉ፡፡ ኮሚቴው በዓመት አንዴ ይሰበሰባል፡፡ የኮሚቴው ስብሰባዎች የሚቆዩበ ጊዜ ተዋዋይ ሀገራት በሚያደርጉት ስብሰባ ይወሰናል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ይሻሻላል፤ በጠቅላላው ጉባኤም እንዲጸድቅ ይደረጋል፡፡
11. የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ኮሚቴው በዚህ ስምምነት የተመለከቱ ሥራዎቹን በብቃት ለማከናወን የሚያስችለውን አስፈላጊ የሰው ኃይልና ዝግጅት ያሟላል፡፡
12. በጠቅላላው ጉባኤ ሲጸድቅና ጉባኤው በሚወስናቸው ሁኔታዎች መሰረት በዚህ ስምምነት የተቋቋመው ኮሚቴ አባላት ከተባበሩት መንግሥታት የአገልግሎት ክፍያ ይቀበላሉ፡፡

## አንቀጽ 44

1. ተዋዋይ ሀገራት በስምምነቱ የተደነገጉትን መብቶች ሥራ ላይ ለማዋል ስለወሰዷቸው እርምጃዎችና በመብቶቹ በመጠቀም ረገድ ስለታየው መሻሻል ቀጥሎ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በኩል ለኮሚቴው ዘገባ ለማቅረብ ተስማምተዋል፡፡

ሀ/ ጉዳዩ በሚመለከተው ሀገር ስምምነቱ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ፤

ለ/ ከዚያ በኂላ በየአምስት ዓመቱ፤

2. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርቡ ዘገባዎች በዚህ ስምምነት የተደነገጉትን ግዴታዎች አፈጻጸም በሚመለከት ያጋጠሙትን ሁኔታዎችና ችግሮች ካሉ መጥቀስ ይኖርባቸዋል። ዘገባዎቹ ጉዳዩ በሚመለከተው ሀገር ውስጥ ስምምነቱ ስላለው ተፈጻሚነት ኮሚቴው አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖረው በቂ መረጃዎች መያዝ አለባቸው።
3. የመጀመሪያውን ዝርዝር ዘገባ ለኮሚቴው ያቀረበ ሀገር በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት የሚያቀርባቸውን ተከታይ ዘገባዎች በሚያቀርብበት ጊዜ ቀደም ሲል ያቀረባቸውን መሰረታዊ መረጃዎች መድገም አያስፈልገውም።
4. ኮሚቴው ለስምምነቱ ተፈጻሚነት አግባብነት ያላቸውን ተጨማሪ መረጃዎች ከተዋዋይ ሀገራት መጠየቅ ይችላል።
5. ኮሚቴው ስለሥራው እንቅስቃሴ በተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ምክር ቤት በኩል ለጠቅላላ ጉባኤው በየሁለት ዓመቱ ሪፖርት ያቀርባል።
6. ተዋዋይ ሀገራት ዘገባዎቻቸውን በሀገራቸው ላሉ ሕዝቦች በሰፊው እንዲዳረሱ ያደርጋሉ።

## አንቀጽ 45

ስምምነቱ በሚገባ ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግና በስምምነቱ በተሸፈነው መስክ ዓለም አቀፍ ትብብርን ለማበረታታት:-

ሀ/ ልዩ የሥራ ኃላፊነት የተሰጣቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መርጃ ድርጅትና ሌሎች የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት የዚህን ስምምነት ድንጋጌዎች ሥራ ላይ ለማዋል በሚደረግ ውይይት ላይ የተሰጣቸውን የሥራ ኃላፊነት በሚመለከት የመወከል መብት ይኖራቸዋል። ኮሚቴው ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸውን የተባበሩት መንግሥታት አካላት፣ የተባበሩት መንግሥታትን የሕፃናት መርጃ ድርጅትና ሌሎች አግባብ አላቸው ብሎ የሚገምታቸውን የድርጅቱን አካላት በየኃላፊነት ድርሻው ስምምነቱን ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የባለሞያ ምክር እንዲሰጡት መጋበዝ ይችላል። ኮሚቴው ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መርጃ ድርጅትና ሌሎች የድርጅቱ አካላት በየሥራ ድርሻቸው ስለ ስምምነቱ ተፈጻሚነት ዘገባዎች እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይችላል።

ለ/ ኮሚቴው ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው አባል ሀገራት የቴክኒክ ምክር ወይም ዕርዳታ እንዲሰጣቸው የሚያቀርቧቸውን ማናቸውንም ጥያቄዎች የራሱን አስተያየት በማከል ልዩ ተልዕኮ ለተሰጣቸው

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች፣ ለተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መርጃ ድርጅትና ለሌሎች አግባብ ላላቸው የተባበሩት መንግሥታት አካላት ያስተላልፋል፡፡

ሐ/ ኮሚቴው የሕፃናትን መብቶች በሚመለከቱ የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ በኮሚቴው ስም ጥናት እንዲደረግ ጠቅላላ ጉባኤው የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊን እንዲጠይቅ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡

መ/ ኮሚቴው በዚህ ስምምነት አንቀጽ 44 እና 45 መሰረት በሚደርሱት መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ አስተያየቶችንና አጠቃላይ የውሳኔ ሃሳቦችን ማቅረብ ይችላል፡፡ እንዲህ ያሉት አስተያየቶችና አጠቃላይ የውሳኔ ሃሳቦች ለማንኛውም ለሚመለከተው ተዋዋይ ሀገር ይተላለፋሉ፤ ለጠቅላላ ጉባኤውም ተዋዋይ ሀገራት ከሚሰጧቸው አስተያየቶች ጋር ሪፖርት ይደረጋሉ፡፡

# ክፍል ሦስት

## አንቀጽ 46

ስምምነቱ ሁሉም ሀገራት እንዲፈርሙት ክፍት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 47

ስምምነቱ መጽደቅ ያስፈልገዋል፡፡ የማጽደቂያዎቹ ሰነዶች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣሉ፡፡

## አንቀጽ 48

ስምምነቱ ማንኛውም ሀገር እንዲቀበለው ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡ የመቀበያዎቹ ሰነዶች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣሉ፡፡

## አንቀጽ 49

1. ሃያኛው የስምምነቱ ማጽደቂያ ወይም መቀበያ ሰነድ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ በተቀመጠ በሰላሳኛው ቀን ስምምነቱ የጸና ይሆናል፡፡
2. ሃያኛው የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ከተቀመጠ በኋላ ስምምነቱን ለሚቀበል ወይም ለሚያጸድቅ ለእያንዳንዱ ሀገር የስምምነቱ ማጽደቂያ ወይም መቀበያ ሰነድ ባስቀመጠ በሰላሳኛው ቀን ስምምነቱ የጸና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 50

1. ማንኛውም ተዋዋይ ሀገር የማሻሻያ ሃሳቦችን ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል። ከዚህ በኋላ ዋና ጸሐፊው የማሻሻያ ሃሳቦቹ ለተዋዋይ ሀገራት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ እንዲሁም በቀረቡት የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ ለመነጋገርና ድምፅ ለመስጠት የተዋዋይ ሀገራት ጉባኤ እንዲዘጋጅ ይፈልጉ እንደሆነ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ይጠይቃል። የማሻሻያ ሃሳቦቹ ለተዋዋይ ሀገራት እንዲደርሱ በተደረገ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ከተዋዋይ ሀገራቱ መካከል ቢያንስ አንድ ሦስተኛው ጉባኤ እንዲዘጋጅ የሚደግፉ ከሆነ ዋና ጸሐፊው በተባበሩት መንግሥታት አዘጋጅነት ጉባኤ ይጠራል። በጉባኤ ላይ ከተገኙትና ድምፅ ከሰጡት ተዋዋይ ሀገራት አብላጫው የደገፉት ማንኛውም የማሻሻያ ሃሳብ እንዲጸድቅ ለጠቅላላ ጉባኤው ይቀርባል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ መሰረት ተቀባይነት ያገኘ የማሻሻያ ሃሳብ በጠቅላላ ጉባኤው ሲጸድቅና ከተዋዋይ ሀገራት መካከል ሁለት ሦስተኛው ሲቀበሉት የጸና ይሆናል።
3. አንድ የማሻሻያ ሃሳብ በሚጸናበት ጊዜ በተቀበሉት ሀገራት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፤ ሌሎች ተዋዋይ ሀገራት በስምምነቱ ድንጋጌዎችና ቀደም ሲል በተቀበሏቸው ማሻሻያዎች ብቻ ይገደዳሉ።

## አንቀጽ 51

1. ሀገራት ስምምነቱን ሲያጸድቁ ወይም ሲቀበሉ ያላቸውን ተአቅቦ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጽሑፍ ተቀብሎ ለሁሉም ሀገራት እንዲደርሱ ያደርጋል።
2. ከዚህ ስምምነት ዓላማዎች ጋር የማይጣጣም ተአቅቦ ተቀባይነት አይኖረውም።
3. ተአቅቦ ለዋና ጸሐፊው በሚላክ ማስታወቂያ በማናቸውም ጊዜ ማንሳት ይቻላል፤ ዋና ጸሐፊውም ይህንኑ ጉዳይ ለሁሉም ሀገራት ያሳውቃል። እንዲህ ዓይነቱ ማስታወቂያ ለዋና ጸሐፊው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ውጤት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 52

አንድ ተዋዋይ ሀገር ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጽሑፍ በማስታወቅ ስምምነቱ እንዳይጸናበት ማድረግ ይችላል። ስምምነቱ እንዳይጸና የማድረጊያው ማስታወቂያ ውጤት የሚኖረው ዋና ጸሐፊው ዘንድ ከደረሰ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው።

## አንቀጽ 53

ስምምነቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣል።

## አንቀጽ 54

የዚህ ስምምነት ዋና ቅጂ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣል፡፡ የአረብኛ፣ የቻይንኛ፣ የእንግሊዝኛ፣ የፈረንሳይኛ፣ የራሺኛና የእስፓኚኛ ቅጂዎች እኩል እውቅና ይኖራቸዋል፡፡